6.4. የምርጫ ዘመቻ አቢይ ኮሚቴ

6.5. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አቢይ ኮሚቴ

6.6. የምርጫ ችግሮች አስወጋጅ አቢይ ኮሚቴ

6.7. የገንዘብ አሰባሳቢ አቢይ ኮሚቴ

6.8. ጽሕፈት ቤት

6.9. ኦዲተር እና

6.10 እንዳስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ሌሎች ኮሚቴዎች

የአመራር አካሎች ተግባርና ኃላፊነት፣ የሥራ አስፈፃሚ አባሎች ተግባርና ኃላፊነት፣ የአመራር አካሎች ስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ፣ ደንቡን ስለማሻሻልና ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ በዝርዝር ከቅንጅቱ «መተዳደሪያ ደንብ» ውስጥ ተካቷል።

7. <u>የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች</u>

7.1 የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)

ስምና ፊርማ

29/02/97 ቀን

7.2 የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ-መድኅን

ስምና ፊርማ

29-02-97 ቀን

7.3 የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ሊግ

ስምና ፊርማ

29-02-97 ቀን

7.2 ቀስተ ደመና የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ

ስምና ፊርማ

[illegible] ቀን

ቀስተ ደመና ኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ

መ/ጠ/12/118/97
2/3/97

ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የፓርቲዎች ቅንጅት መቋቋሙን መግለፅና እውቅና መጠየቅ</u>

- ➢ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/
- ➢ ኢዴአፓ-መድኅን
- ➢ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ
- ➢ ቀስተ ደመና የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ በጋራ ሆነው ያቋቋሙት «ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ» በአጭሩ ሲጠራ «ቅንጅት» በእንግሊዝኛ «Coalition For Unity and Democracy (CUD)» የሚል ቅንጅት አቋቁመናል፤

ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት በአገር ውስጥ ሕጋዊ ዕውቅና አግኝተው በሰላማዊ ትግል ሕዝቡን በማደራጀት ላይ የሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች ቅንጅቱን ሲያቋቁሙ የተስማሙበትን - የመመስረቻ ሰነድ (መሰስተኛ ፕሮግራም) እና

- የመተዳደሪያ ደንብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሆኖ ተልኳል፤

የቅንጅቱ የመመሥረቻ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ የፖለቲካ ድርጅቶቹ በጋራ የሚመሩበት እንደመሆኑ በሰነዶቹ መሠረት መጪውን ብሔራዊ ምርጫ በቅንጅቱ መሪነት ለመንቀሳቀስ የወሰንን መሆኑ ታውቆ ቅንጅቱ ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ ይደረግ ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

<u>ምዝገባ የጠየቀው ቅንጅት አባል ድርጅቶች</u>

1. የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት — ኃይሉ ሻውል, HAILU SHAWEL, AEUP PRESIDENT
2. ኢዴአፓ-መድኅን — ሊቀመንበር
3. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ
4. ቀስተደመና የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ

ቀስተ ደመና ኢትዮጵያ
የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ

ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)